የሰ/መ/ቁ. 57938

ሐምሌ 14/2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** 1- አቶ አደም አብዱ } የቀረበ የለም

2- አቶ ጀማል አሊ

**ተጠሪ፡-** የፌደራል ሥነ - ምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ሕግ

ዋልተንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካቶች በተከሠሡበት የሙስና ወንጀል የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ መካከል የነበረውን የቅድመ ክስ ክርክር ሂደት ከሠማ በኋላ ወደ ዋና ክስ እንዲገባና የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች እንዲሠሙ የመወሰኑን እና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይሄንኑ ትዕዛዝ የማፅናቱን አግባብነት ለመመርመር የቀረበ ነው፡፡

አመልካቾች ቅሬታቸውን ከሌሎች 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች ከነበሩት እና ጉዳያቸው አያስቀርብም ከተባሉት ጋር ያቀረቡ ሲሆን ሰኔ 23 ቀን 2002 ዓ.ም በ3 ገፅ በተፃፈ አቤቱታ የአሁን አመልካቾችን የሚመለከተው ክፍል ፍሬ ሃሣብ ከሣሽ የአሁን አመልካቾችን ከገቢያቸው በላይ ንብረት አፍርተዋል በማለት ስለተከሣሾቹ የያዘው የሀብት ማስረጃ ሣይኖር በወ/መ/ሕግ ቁ 419/ለ/ መሠረት ክስ ማቅረቡ ያለአግባብ ነው በሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በቀን 21/4/2003 ዓ.ም በሁለት ገፅ የሠጠው የመልስ ፍሬ ሃሣብ አመልካቾች የሉሲ አንጅነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር አባል ብቻ ሣይሆኑ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ውስጥ ባላቸው ኃላፊነት በመጠቀም ማህበሩ ያለአግባብ ጨረታዎቹን እንዲያሸንፍ አድርገዋል፡፡ ከገቢያቸው ጋር ያልተመጣጠነ ንብረት አፍርተዋል በማለት የከሰሰ ሲሆን ወደ ክሱ ሲገባ በማስረጃ ነጥሮ የሚወጣ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ወደ ዋና ክስ እንድንገባ መወሰኑ በአግባቡ በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ

መርምሮታል፡፡ በዚሁ መሠረት የወንጀል ጉዳዩን እየተመለከተ ያለው ፍርድ ቤት የቅድመ ክሱን ክርክር በመስማት ወደ ዋናው ክስ ተገብቶ ምስክር እንዲሠማ መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህ መሠረት በሙስና ወንጀሎች ላይ የቅድመ ክስ ዝግጅት የሚመራበት አግባብ በአዋጅ ቁ 434/97 አንቀጽ 35 እስከ 41 ድረስ የተዘረዘሩ ሲሆን ሂደቱ ውስጥ ማለፍ አስገዳጅ ያልሆነና እንደ ክሱ ዓይነት ታይቶ የክሱ ጭብጦችና ማስረጃው ዝርዝር ውስብስብ በመሆኑ የፍርድ ሂደቱን ሊያራዝምና ሊያወሣስብ ይቻላል ብሎ ፍርድ ቤቱ ሲገምት ሊያዝ የሚችል ስለመሆኑ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 35 በግልፅ ያስቀምጣል፡፡

የቅድመ ክስ ዝግጅት ዓላማ ለክሱ አወሣሠን ሊረዱ የሚችሉ ጭብጦችን ለመለየት ፣ ባለጉዳዮች ጭብጦችን እንዲረዱ ማድረግ ፣ የክሱን ሂደት ለማፋጠንና ችሎቱ አካሄዱን ለመምራት እንዲችል ለማስቻል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁ 434/97 አንቀጽ 36/1/ ሥር የተዘረዘረ ሲሆን የማስረጃዎች ተቀባይነት ላይ እና መደበኛው ክስ ከመጀመሩ በፊት ውሣኔ ሊያገኙ በሚገባቸው የህግ ጥያቄዎች ላይ ውሣኔ የሚሠጥ ስለመሆኑ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 36/2/ ሥር ተደንግጓል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች ከገቢያቸው በላይ ንብረት አፍርተዋል በማለት የተከሠሡ በመሆኑ ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት የቅድመ ክሱን ሂደት ካዳመጠ በኋላ ወደ ዋና ጉዳዩ ተገብቶ ምስክሮች ይሠሙ በማለት ትዕዛዝ መስጠቱ በአመልካቾች ላይ ከቀረበው ክስ አኳያ ሲታይ የተከሠሱበት ጉዳይ በማስረጃ የሚጣራ ከመሆኑ አኳያ ተፈፀመ ሊባል የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡ በተጨማሪም በዚህ ቅድመ ክስ ዝግጅት ሂደት ውስጥ መታለፍ ራሱ አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ የተቀመጠ ባለመሆኑና ፍርድ ቤቱ የጉዳዩን ውስብስብነት እየተመለከተ የሚወሰነው ጉዳይ በመሆኑ የቀረበው የወንጀል ክስ በማስረጃ እንዲጣራ መታዘዙ ቅሬታ የሚቀርብበት ሊሆን አይገባም ብለናል፡፡ በዚሁ መሠረት የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ዋና ክስ ተገብቶ ምስክሮች ይሠሙ በማለት የሠጠው ብይን እና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሠጥተናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 54774 ሰኔ 11 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 85874 መጋቢት 09 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጡት ውሣኔ በተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና ማስረጃ ህግ አዋጅ ቁ 434/97 አንቀጽ 40 መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የቅድመ ክስ ዝግጅት ሂደት እንደተጠናቀቀ በወንጀል ክሱ የተመለከቱት ነጥቦች ላይ ምስክሮች እንዲሠሙ መታዘዙ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ